የሰ/መ/ቁ. 44862

ጥር 5 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** አሸናፊ አበበ - ጠበቃ ኒቆዲሞስ ጌታሁን ቀረበ

**ተጠሪ፡-** የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ - ታደለ ተስፋዬ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጉምሩክን ሕግ በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሞአል በማለት ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበውን ክስ መነሻ በማድረግ የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ አመልካች እና በወቅቱ ሁለተኛ ተከሣሽ የነበረው ታደለ ገብሬ ኪዳኔ የተባለው ግለሰብ የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሰራርን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 228 እና 66/2/ ላይ የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ የጉምሩክ ሥነ-ሥርአት ያልተፈጸመባቸውን አልባሳት ይዘው የማስተላለፍ ወንጀል ፈጽመዋልና ቅጣት ይወሰንባቸው በማለት ጠይቆአል፡፡

ተከሣሾቹ ለክሱ በሰጡት መልስ በክሱ የተነገረውን ድርጊት አልፈጸምንም፤ ጥፋተኛም አይደለንም በማለት በመከራከራቸው ፍ/ቤቱ በዓቃቤ ሕጉ የቀረቡትን ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ ተከሣሾች ሊከላከሉ ይገባል በማለት ብይን ሰጥቶአል፡፡ በዚህ መሰረትም የመከላከያ ማስረጃዎች የሰማ ሲሆን፣በመጨረሻም ተከሣሾች እንደክሱ አቀራረብ ተመስክሮባቸዋል፡፡ ለማስተባበልም አልቻሉም በማለት በተጠቀሰባቸው ሕግ መሰረት ጥፋተኞች ናቸው ብሎአቸዋል፡፡ ሲያስተላልፉት የተገኘው አልባሳት እንዲወረስ፣ለአልባሳቱ ሊከፈል ይገባ የነበረው የቀረጥና ታክስ መጠን በሚያህል ገንዘብ ብር 10,520.33(አስር ሺህ አምስት መቶ ሃያ ብር ከሠላሣ ሦሥት ሣንቲም) ለመንግስት እንዲከፍሉ እና በአስራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኖባቸዋል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን የሰማ ሲሆን፣በመቀጠልም ይግባኝ የተባለበትን ውሳኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች መጋቢት 28 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ለተፈጸመው ድርጊት በአቃቤ ሕግ የተጠቀሰው የአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 66/2/ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ዓቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ የጠቀሰው ድንጋጌ አግባብነትን ለመመርመር የክስ ቻርጁን ይዘት ማየት አስፈላጊ በመሆኑ ተመልክተነዋል፡፡ በቻርጁ ላይ የተገለጸው አመልካች አልባሳቱ ተጭነው የተገኙበትን መኪና

ሲያሽከረክር እንደነበር፣አብሮ የተከሰሰው ታደለ ገብሬ ኪዳኔ የተባለው ደግሞ አልባሳቱን ያስጫነ እንደሆነ፣ መኪናው የመጣው ከናዝሬት መስመር ወደ አዲስ አበባ ሲሆን፣አመልካች አቃቂ የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ኬላ ላይ እንደደረሰ የጉምሩክ ሰራተኞች ለፍተሻ እንዲቆም ሲጠይቁት ኬላውን ጥሶ መሄዱን፣በኋላም በተደረገው ክትትል በተለምዶ ሃና ማሪያም አካባቢ ተይዞ ፍተሻ ሲደረግ አልባሳቱ መገኘታቸውን ነው፡፡ ዓቃቤ ሕግ ባቀረባቸው ማስረጃዎች ልክ እንደ ክሱ እንዳስረዳ አቤቱታ በቀረበበት ውሳኔ ተመልክቶአል፡፡ በክሱ የተጠቀሰው የጉምሩክ አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 66/2/ የኮንትሮባንዱ ድርጊት/ጥፋት/ የተፈጸመው ሃይል በመጠቀም ወይም ከሌሎች ጋር በማበር ሆኖ በተገኘ ጊዜ የሚጠቀስ እንደሆነም ከድንጋጌው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በመሆኑም መጠቀሱ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ አቤቱታ በቀረበበት ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 136351 ጥር 18 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 76902 መጋቢት 7 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሕግ ሥ/ቁ. 195/2/ለ/2/ መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. አመልካች ያቀረበው የሰበር ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

   መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ